

# የሴት ልጅ ግርዛት በኢትዮጵያ:

## ወቅታዊ ቁልፍ ግኝቶች

ሰኔ 2015

28 TOO MANY
FGM... let's end it.

ORCHID PROJECT

***ይህ የሀገር መግለጫ መረጃ በኢትዮጵያ (2015/16) ስለ ሴት ልጅ ግርዛት/ብልት ትልተላ (FGM/C) ወቅታዊ ሁኔታዎች እና መረጃዎች ላይ ሰፊ መረጃ ይሰጣል። እንዲሁም የወቅቱን የፖለቲካ ሁኔታና ይህንን ተግባር እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል የሚያሳዩ የህግ ማዕቀፎችን እና መርሃ ግብሮችን ትንተናና ምክሮችን መስጠትን ያካትታል። ይህ ሪፖርት የ2013 (28 Too Many's 2013 Ethiopia Country Profile.) ማሻሻያ ሆኖ ያገለግላል። ዓላማውም በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ላይ እጅግ የተሻለውን ወቅታዊ መረጃ በማዘጋጀት አክቲቪስቶችን፣ ባለሙያዎችን፣ የልማት አጋሮችን እና የምርምር ድርጅቶችን በፖሊሲ እና በተግባር ላይ የውሳኔ አሰጣጥን ለማሳወቅ ነው።***

# ምን እየጠፈጠረ ነው?

በኢትዮጵያ የሴት ልጅ ግርዛት ስርጭት እየቀነሰ ያለ ይመስላል። እንደ DHS ዘገባዎች በ1992 ከ15-49 ከነበሩት 79.9% ሴቶች በ1997 ወደ 74.3% እና በ2008 ወደ 65.2% ዝቅ ብሏል።

ሆኖም የኢትዮጵያ ህዝብ ቁጥር እየጨመረ በመምጣቱ ለአደጋ የተጋለጡ ልጃገረዶች ቁጥር ጨምሯል።


ከ2016 ጀምሮ በኢትዮጵያ እስካሁን 33 ሚሊዮን ልጃገረዶች እና ሴቶች ለአደጋ ተጋላጭ እንደሆኑ የኦርካይድ ፕሮጀክት ግምት ያሳያል። ይህም በምስራቅ እና ደቡባዊ አፍሪካ ውስጥ እጅግ ትልቁ የልጃገረዶች/ሴቶች ቁጥር ሲሆን በአለም አቀፍ ደረጃ ከኢንዶኔዥያ እና ግብፅ ቀጥሎ ሶስተኛው ነው።

# የሴት ልጅ ግርዛት የት ነው የሚከናወነው?

በምስራቅ ኢትዮጵያ (ሶማሌ እና አፋር) ከፍተኛ የሴት ልጅ ግርዛት ስርጭት ሲኖር ዝቅተኛው ደግሞ በትግራይ ሰሜናዊ ክልል ውስጥ ነው። ነገር ግን የህዝብ ብዛትን ከግምት ውስጥ በማስገባት ከ60% በላይ የሚሆኑት በግርዛት የተጠቁ ሴቶች እና ልጃገረዶች የሚኖሩት በኦሮሚያ (ዘጠኝ ሚሊዮን) እና በአማራ (ሰባት ሚሊዮን) ክልሎች ነው።[2]

ከ1992 እስከ 1998 ባለው ጊዜ ውስጥ ከፍተኛው መሻሻል/የስርጭት ቅነሳ የታየው በድሬዳዋ (95.1% ወደ 75.3%)፣ በአማራ (79.7% ወደ 61.7%) እና በአዲስ አበባ (79.8% ወደ 54%) ነው። ዝቅተኛ መሻሻል ያስመዘገበው ክልል ሱማሌ ነው (99.7% ወደ 98.5%)።

ከ1992 እስከ 1998 ባለው ጊዜ ውስጥ ትግራይ፣ ደቡብ ክልል፣ ኦሮሚያ፣ ድሬዳዋ፣ ሀረሪ፣ አዲስ አበባ፣ አማራ እና ቤንሻንጉል ጉሙዝ ከ15-49 ዓመት ክልል ውስጥ የሴት ልጅ ግርዛት ከ10 በመቶ በላይ ቀንሷል። በአፋር ውስጥ ያለው ስርጭት በ 7% ብቻ ቀንሶ አሁንም ከፍተኛው (91.2%)[3]ነው።





*በኢትዮጵያ በሴቶች ላይ የሚደርሰው የግርዛት ስርጭት እና በሴት ልጅ ግርዛት የተጠቁ ልጃገረዶች እና ሴቶች ቁጥር በእያንዳንዱ ክልል*[4]

# እንዴት ነው የሴት ልጅ ግርዛት እየተከሰተ ያለው?

ከ15-49 ዓመት ከሆናቸውና የሴት ልጅ ግርዛት እንደ ተፈጸመባቸው ሪፖርት ከተደረጉት ኢትዮጵያውያን ሴቶች መካከል 73% የሚሆኑት ሴቶች አካላቸው ተቆርጦ ተወግዷል። 2.6% ያህሉ እንደ የተቆረጡ ሲሆን፣ ነገር ግን ሥጋቸው አልተወገደም፤ እና 6.5% 'የተሰፉ' (የተሰፋ ወይም የዓለም ጤና ድርጅት በወጣው ደረጃ መሰረት 3ኛው ዓይነት) ሪፖርት ተደርጓል። 17.9% የሚሆኑት ደግሞ ምን አይነት የሴት ልጅ ግርዛት እንደተደረገባቸው አያውቁም።[5]

የተሰፉ ሴቶች እና ልጃገረዶች በብዛት ከሰማሌ(75.6%) እና ከአፋር (71%) ብሄረሰቦች የተውጣጡ ናቸው፤ ከ15-49 አመት እድሜ ያላቸው ሴቶች ናቸው።

ሙስሊም ሴቶች ከሌላ እምነት ተከታዮች በበለጠ የመገረዝ እድላቸው ሰፊ ነው።.[6]




*ዕድሜያቸው ከ15-49 የሆኑ ኢትዮጵያውያን ሴቶች የግርዘት ዓይነቶቻ*

## ግርዛት የሚደረግበት እድሜ

በኢትዮጵያ ውስጥ አብዛኛው የግርዛት ሂደት የሚከናወነው አምስት ዓመት ሳይሞላቸው ነው፤ ነገር ግን አንድ አምስተኛ የሚሆነው ከአምስት እስከ ዘጠኝ ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ነው፤ ይሁን እንጂ ይህ አንደየሃይማኖቶች, የመኖሪያ አካባቢዎች እና ጎሳዎች ይለያያል።

በእያንዳንዱ የኢትዮጵያ ክልል (ከ15-49 ዓመት የሆኑ ሴቶችን) መሰረት ያደረገ የግርዛት እድሜን ማጥናት በየክልሉ ያሉ ልጃገረዶች የተጋላጭነት እድሜ ያሳያሉ።

- በትግራይ፣ አፋር እና አማራ ያሉ ሴት ልጆች ከተወለዱ ብዙም ሳይቆዩ ነው ለዚህ የግርዛት አደጋ ተጋላጭ የሚሆኑት።
- በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ልጃገረዶች እስከ አንድ አመት ድረስ ለግርዛት አደጋ የተጋለጡ ናቸው። ይህ ማለት ለውጥ ለማመምጣት በነፍሰ ጡር ሴቶች እና ገና እርጉዝ ባልሆኑ ወጣቶች ላይ ያነጣጠረ መርሀግብር መካሄድ አለበት።
- በኦሮሚያ ያሉ ልጃገረዶች ከተወለዱ ጀምሮ እስከ 11ኛ ዓመት ዕድሜያቸው ድረስ ለግርዛት አደጋ የተጋለጡ ሲሆኑ በድሬዳዋ ሴት ልጆች ከተወለዱ ጀምሮ እስከ አሥር ዓመት ዕድሜያቸው ድረስ ለአደጋ የተጋለጡ ናቸው።
- በጋምቤላ ልጃገረዶች ለግርዛት አደጋ የተጋለጡት ገና አምስት ዓመት ሳይሞላቸው ሲሆን፣ በአዲስ አበባ ደግሞ አራት ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ ነው።
- በሶማሌ ክልል ልጃገረዶች ከስምንት እስከ አሥር ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ እና በሐረሪ ከሰባት እስከ አሥር ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ለግርዛት በጣም የተጋለጡ ናቸው።8

## የድርጊቱ ፈፃሚዎች

እድሜያቸው ከ0-14 የሆኑ ኢትዮጵያውያን ልጃገረዶች ማለትም የሴት ልጅ ግርዛት ከተፈጸመባቸው 95.3 በመቶው የተገረዙት በባህላዊ ገራዦች ሲሆን፤ ነገር ግን አልፎ አልፎ በልምድ አዋላጆች (2.2%) ወይም በሕክምና ባለሙያዎች (1.9%) ነው።[9]

በህክምና ተቋማት ይደረግ የነበረው የሴት ልጅ ግርዛት በኢትዮጵያ መንግስት በ1999 ዓ.ም ታግዷል፤ ግርዛትን የሚፈጽሙ የህክምና ባለሙያዎች ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው አድርጓል።[10] ነገር ግን በደቡብ ክልል ግርዛት ከተፈጸመባቸው ሴቶች መካከል 10 በመቶ የሚሆኑት የሴት ልጅ ግርዛት የተከናወነው በጤና ባለሙያዎች ነው። ይህም ከአገር አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ልዩነት ነው።[11]

# ለምንድን ነው አሁንም ግርዛት እየተካሄደ ያለው?

በኢትዮጵያ ውስጥ የብሔር ማንነት እና ማህበራዊ ትስስር የሴት ልጅ ግርዛት ሂደት ጠንካራ ሞተር ናቸው። ብሄር ከሀይማኖታዊ መስተጋብር ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ስለሆነም የሴት ልጅ ግርዛት ያስፈልጋል የሚለው የተሳሳተ እምነት በዋናዎቹ ሃይማኖቶች ዘንድ የተለመደ ነው።

የሴትን ልጅ ግርዛት አስከፊነት የሰሙ 17.5% ሴቶች እና 11.1% ወንዶች (ከ15-49 እድሜ ያላቸው) **ድርጊቱ መቀጠል እንዳለበት** ያምናሉ። 79.3% ሴቶች እና 86.7% ወንዶች ደግሞ **መቀጠል እንደሌለበት ያምናሉ።**[12]


ከ15-49 አመት የሆናቸው 23.6% ሴቶች እና 16.8% ወንዶች ግርዛት የሃይማኖታቸው መስፈርት እንደሆነ አድረገው ያምናሉ። ይህ እምነት በሙስሊም ወንዶችና ሴቶች ዘንድ በብዛት ይታያል።[13]

ለሴት ልጅ ግርዛት በጣም ጠንካራ ደጋፊ የሆኑት የአፋር፣ የሰማሌ እና የሲዳማ ሴቶች እና የአፋር፣ የሰማሌ እና የአማራ ወንዶች ናቸው።[14]

ነገር ግን በተዘዋዋሪ መንገድ የአጠያየቅ ዘዴዎችን በመጠቀም በተደረጉ ትንንሽ ጥናቶች ላይ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በቀጥታ ሲጠየቁ ለግርዛት የሚሰጡት ድጋፍ ዝቅተኛ መሆኑን ሲገልጹ፤ በተዘዋዋሪ ሲጠየቁ ግን የድጋፉ መጠን በላቀ ደረጃ ከፍ ያለ መሆኑን ያሳያል።[15]

እንደዚህ ያለው ጥንቃቄ የሚፈልግ፣ ሚስጥራዊነትን የተላበሰ እና በማህበረሰቡ ዘንድ በግልጥ ለማውረት ያልተፈቀዱ ጉዳዮች በሚመረምሩበት ጊዜ **የተሻሻሉ የዳሰሳ ጥናት ዘዴዎችን** አስፈላጊነት ያጎላሉ።

በሀገሪቱ ውስጥ ባሉ ግርዛት በሚካሄድባቸው ቦታዎች **ተግባራዊ እርምጃዎች** መከናወን አለባቸው። በአብዛኞዎቹ ጉዳዮች ላይ የድርጊቱ ጠንከር ያሉ አራማጆች የሃይማኖታዊ ልምምዶች ናቸው። ስለዚህ እነዚህ ቦታዎች ላይ ለማስተማር እና አመለካከትን ለመቀየር የሀይማኖት አባቶችን ማሳተፍ ወሳኝ ነው።




*. ከ15-49 ዕድሜ ክልል ውስጥ ባሉ ኢትዮጵያውያን ሴቶች ላይ የሴት ልጅ ግርዛት መስፋፋት ከብሔር አንፃር*[16]

በተለይም የሴት ልጅ ግርዛት ለጋብቻ ብቁ ከመሆን እና ከንጽህና ጋር የተቆራኘ ስለሆነ በሚያሳዝን ሁኔታ አሁንም በአንዳንድ የኢትዮጵያ ማህበረሰቦች ዘንድ የሴትን ልጅ ግርዛት አለመፈጸም አሉታዊ ተጽዕኖ አለው። አብዛኛዎቹ ልጃገረዶች እና ሴቶች እነዚያን መዘዞች ለማስወገድ ሲሉ የሴት ልጅ ግርዛትን ለመፈፀም ይነሳሳሉ። [17]

የሚከተሉት ምክንያቶች በኢትዮጵያ የሴት ልጅ ግርዛት ስርጭት ላይ ተፅዕኖ የሚሳድሩ ናቸው።

*ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ፡-* የሀብት ክፍፍሉን በመቶኛ መሰረት ስናይ በዝቅተኛውና ከፍተኛው ስርጭት መካከል ያለው ልዩነት የሰፋ ነው። በ1992 ዓ.ም ከፍተኛ እና አነስተኛ የሴት ልጅ ግርዛት ባለባቸው መካከል የ6.2 በመቶ ያህል ብቻ ነበር ልዩነቱ (መካከለኛው 76.7 በመቶ እና ዝቅተኛው 82.9 በመቶ) ፤ በ2016 ግን ልዩነቱ ወደ 14.7 በመቶ ከፍ ብሏል። (56.7% የበለጸጉ እና 71.4% የመካከለኛው) ። በመካከለኛው ክፍፍል ውስጥ ያለው ስርጭት በጣም የተረጋጋ ሲሆን በዝቅተኛው እና ከፍተኛው ሀብት ክፍፍል ልምምዱ ብዙም ያልተለመደ ነው።[18]

*ትምህርት* ፡ ትምህርት በኢትዮጵያ ካለው የሴት ልጅ ግርዛት ስርጭት ጋር የተያያዘ ይመስላል። (ከ15-49 አመት እድሜ ያላቸው) መደበኛ ትምህርት ከሌላቸው ሴቶች ይልቅ የሁለተኛ ደረጃ እና የመገረዝ እድላቸው አነስተኛ ነው።በዚሁ መሰረት ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ያላቸው ሴቶች 19.9%፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ያላቸው 50.6% እና ያልተማሩ ሴቶች 72.9% የመገረዝ እድል አላቸው።.[19]

*የመኖሪያ ቦታ:* ከ1992 ዓ.ም እስከ 1998 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በገጠር ከነበረው ስርጭት በበለጠ ፍጥነት ከተሞች የግርዛት ስርጭት ቀንሷል። በ 1998 ዓ.ም በከተማ ያለው ስርጭት 53.9% ፣ በገጠር ደግሞ 68.4% ነበር።[20]

*ህዝባዊ እና ፖለቲካዊ አለመረጋጋት:* ኢትዮጵያ በታሪኳ ብዙ ፖለቲካዊ እና ባህላዊ ውዝግቦችን አስተናግዳለች፤ በቅርቡ በሰሜን ትግራይ ክልል ከ2012 እስከ 2014 ድረስ በቆየው ውዝግብ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን እና የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ኮሚሽነር[21] ፅህፈት ቤት ዓለም አቀፍ የሰብአዊ/የስደተኞች መብቶች ጥሰት እና የጦር ወንጀሎች ማስረጃ አግኝተዋል።[22] በተጨማሪም በጥር 2015 ዓ.ም እምነታቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ እንዲያካሂዱ በሚገፋፉ መሪዎች ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተገንጥሎ በተቋቋመው አዲስ ሲኖዶስ ምክንያት ብጥብጥ ተቀስቅሷል።[23] ብጥብጦች እና አለመረጋጋት በሴቶች እና ልጃገረዶች መብቶች ላይ፣ በውሳኔ ሰጪነታቸው እና በአጠቃላይ የአንድ ሀገር እድገት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ያስከትላሉ፤ በዚህ ምክያትም ለምሳሌ ያህል የትምህርት ቤቶች መዘጋት፣ እንደ አስገድዶ መድፈር ያሉ የጦር ወንጀሎች፣ የጤና አገልግሎቶች እና እርዳታዎች መስተጓጎል እና አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ አለመረጋጋት ተከስቷል።

# ዋና ዋና ተግዳሮቶች

## ሀ. ትኩረት መጨመር

የኢትዮጵያ መንግስት በ2017 ዓ.ም.24 የሴት ልጅ ግርዛትን ለማጥፋት ትልልቅ ዕቅዶችን ይዟል።.[24]

ነገር ግን ከገንዘብ አኳያ ተገቢው ትኩረት ካልተሰጠ እና እድገት ካልተፋጠነ የ 2022 ዓ.ም የእድገት ግቦች ላይ መድረስ እንኳን የማይቻል ነው።

የኢትዮጵያ መንግስት የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስወገድ የሚያስችል ሁኔታን ለመፍጠር የሴት ልጅ ግርዛትን በወንጀለኛ መቅጫ ህግ[25] ውስጥ በመክተት እና ያለእድሜ ጋብቻን እና የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቆም ሀገራዊ ወጪ የተደረገበት ፍኖተ ካርታ አዘጋጅቷል።[26]

በዚያ ፍኖተ ካርታ ላይ መንግስት እነዚህን ሁለት ልምምዶች ለማስወገድ የበጀት ድልድሉን በ10% ለማሳደግ ወስኗል። ነገር ግን መንግስት የገባውን ቃል ለመፈፀም የገንዘብ መጠንን ቢጨምርም ከ2022 ዓ.ም ከታቀደው (ዘላቂ የልማት ግብ 5) አስቀድሞ የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስወገድ ከፍተኛ እድገት ያስፈልጋል። ግስጋሴው አሁን ካለው የስርጭት መቀነስ ከሰባት እጥፍ በላይ መፋጠን አለበት።[28]

## ለ. ትክክለኛውን የህዝብ ብዛት መረጃ መጠቀም

በኢትዮጵያ ያለው የህዝብ ብዛት በጣም ብዙ በመሆኑ በክልላዊ ደረጃ የሴት ልጅ ግርዛት ስርጭትን በተመለከተ መረጃ በበቂ ሁኔታ ተግባራዊ እርምጃ ለመውሰድ አጥጋቢ አይደለም። በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጪ የተደረገበት ያለእድሜ ጋብቻ እና የሴት ልጅ ግርዛት ፍኖተ ካርታ ላይ እንደተመከረው በዞንና በወረዳ ደረጃ ያሉ የንዑስ ክልላዊ መረጃዎች በክልሎች ውስጥ ያሉ ቦታዎችን በመለየት ያሉትን ሀብቶች በአግባቡ ለመጠቀም ቢያስፈልግም የመረጃው ደረጃ እስካሁን አልተገኘም።[29]

ምንም እንኳን የሴት ልጅ ግርዛት ስርጭት በሶማሌ እና በአፋር ክልል ከፍተኛ ቢሆንም፣ በክልሎቹ ያለው ህዝብ ብዛት ግን ዝቅተኛ ስርጭት ካላቸው ሌሎች ክልሎች ያነሰ ነው። እንደሚገመተው የአፋርና የሶማል ክልል ከሌሎቹ ጋር ሲወዳደር፣ በአማራ ክልል ብቻ ሰባት ሚሊዮን ሴቶችና ልጃገረዶች፣ በኦሮሚያ ክልል ደግሞ ዘጠኝ ሚሊዮን ሲሆኑ በአፋር ክልል 790,000፣ በሶማሌ ሁለት ሚሊዮን ነው።.[30]

## ሐ. በድብቅ የሚደረግ የሴት ልጅ ግርዛት

በኢትዮጵያ ጠንካራ የህግ እና የፖሊሲ ማዕቀፎች እና በማህበረሰብ አቀፍ ደረጃ በሴት ልጅ ግርዛት ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የማህበረሰብ አቀፍ ማዕቀቦችን ለማስቀመጥ የሚደረጉ ጥረቶች ድርጊቱን በድብቅ እንዲደረግ የሚገፋፉ እና በምርምር ውጤቶች ላይ የማህበራዊ ፍላጎት አድሎአዊነትን አሳድገዋል። አዳዲስ የምርምር ዘዴዎች በመጠን ተረጋግጠው ምላሽ ሰጪዎችን 'እውነተኛ' ሆነው በታማኝነት በሴት ልጅ ግርዛት ላይ ያላቸውን አመለካከት ለመመርመር ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው።

በኢትዮጵያ ለሴት ልጅ ግርዛት የተሰጡ ምላሾች ግንዛቤን መፍጠር ላይ ያተኮሩ ናቸው፤ ይኸውም ትምህርት በትምህርት ቤቶች፣ በሴቶች ክለብ ውስጥ ልጃገረዶች ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችንና ውጤቶቻቸውን መወያየታቸው እና የሴቶች ሰብአዊ መብቶችን በማህበረሰብ ዘመቻዎች ላይ መንፀባረቅ ናቸው። ይህም ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ባላቸው ሴቶች እና ልጃገረዶች፣ በከተሞች እና በከፍተኛ የሀብት ክፍፍል ውስጥ ያለው ስርጭት እንዲቀንስ አድርጓል።

ነገር ግን በኦሮሚያ[31] እና በአፋር,[32] ሰተዘዋዋሪ የጥያቄ አጠያየቅ ዘዴዎችን በመጠቀም ስለ ሴት ልጅ ግርዛት አመለካከቶችን እና ልምዶችን ለመዳሰስ በተዘዋዋሪ መንገድ ምላሽ የሰጡ ሰዎች በቀጥታ ከተጠየቁት ይልቅ ለድርጊቱ ያላቸውን ድጋፍ ገልጸዋል። እነዚህ ጥናቶች የተካሄዱት በተወሰነ አካባቢ (ትንሽ ማህበረሰቦች ላይ በአንድ ክልል ውስጥ ብቻ ነው)፤ ነገር ግን የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻዎች እና ጠንካራ የህግ ማዕቀፎች ሊያስከትሉ የሚችሉትን አሉታዊ ተፅእኖ ያመለክታሉ። ድርጊቱን በድብቅ እንዲደረግ እንዳይገፋፋቸው እና ስለ ሴት ልጅ ግርዛት በሚደረጉ ውይይቶች ላይ ሰዎች ያላቸውን አመለካከት እና እምነት የሚነኩ ጥያቄዎች ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። እነዚህ ቀጥተኛ ያልሆኑ ዘዴዎች በተጨባጭ እንዴት እንደሚሠሩ ለማወቅ ተጨማሪ ምርምር ያስፈልጋል።

.

## መ. ባህላዊ ትውፊቶች

በኢትዮጵያ ያለው የሴት ልጅ ግርዛት ከባህል ከጋብቻና ከብሔር ማንነት ጋር በእጅጉ የተያያዘ ነው። ተግባራዊ እርምጃው ለእነዚህ ትስስሮች በፈጠራ መንገዶች ምላሽ መስጠት አለበት፤ እናም የወንዶች እና የወጣት ወንዶች በፕሮግራሙ ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ ወሳኝ ነው። በኢትዮጵያ ያለው የሴት ልጅ ግርዛት እንደየ ብሄሩ እና እንደየ ሀይማኖታዊ ትስስሩ እንዲሁም መልክዓ ምድራዊ አቀማመጡ በስፋት ይለያያል።
ልክ አሽከርካሪዎች በቡድን መካከል እንደሚለያዩ ሁሉ ይህም ጉዳ ውጥረትን ፈጥሯል፤ ስርጭቱ ከአገር አቀፍ አማካይ እጅግ የላቀ እና የፕሮግራም አወጣጡ ላይ ፈተና የሚፈጥርበት ነው።.[33]

ከመረጃው መረዳት የሚቻለው በኢትዮጵያ ውስጥ የጋብቻና የብሔር ተዋጽኦዎች ቀዳሚዎቹ የሴት ልጅ ግርዛት አሽከርካሪዎች መሆናቸውን ነው። ስለዚህም ነው አንዳንድ ልጃገረዶች ከእኩዮቻቸው ጋር ትዳር መሥርተው ልጅ መውለድ እንዲችሉ በሚል ሰበብ ወላጆቻቸው እንዲያስገርዟቸው እንደሚማጸኑ ይነገራል።[34] ለብዙ ኢትዮጵያውያን ልጃገረዶች ያልተገረዙ መሆናቸው ጉልህ የሆነ ማህበራዊ አደጋዎችን ያመጣል። ለአንዳንድ ሙስሊም ልጃገረዶች አለመገረዝ ከሃዲ/ከዳተኛ ወይም ሙስሊም ካልሆኑት ጋር እኩል የሚያደርግ ነው። ለሌሎች ደግሞ ማግባት አለመቻል ማለት ሲሆን ይህም በኢኮኖሚ እና በማህበረሰብ ንብረት ላይ ከፍተኛ አደጋን ይፈጥራል።[35]

በኢትዮጵያ ያልተገረዙ ልጃገረዶች ላይ የሚደርሱትን ማህበራዊ ተጽዕኖዎች ለመቀነስ፣ ለደርጅቶችና እና ለውሳኔ ሰጪነት የበለጠ እድል ለመፍጠር ያለመ ፕሮግራም መኖሩ ወሳኝ ነው። በትዳር ውስጥ ያልተገረዙ ልጃገረዶችን ተቀባይነት ለማሳደግ ከወንዶች እና ወጣት ወንዶች ጋር መስራት ተጨማሪ ትኩረት የሚያስፈልገው ቁልፍ የፕሮግራም መስክ ነው።

## ሠ. አስተማማኝ ገቢ አለመኖር

ጎጂ ባህላዊ ልምምዶችን የሚቃወሙ ልጃገረዶች አስተማማኝ ገቢ ያለመኖር ከፍተኛ ውጥረትን ይፈጥራል። እነዚህ ልጃገረዶች በማህበራዊ ህይወታቸው መገለል፣ ለበለጠ ኢኮኖሚያዊ አለመረጋጋት እና በአንዳንድ ሁኔታዎች ለሞት ይጋለጣሉ። ፕሮግራሙ የሴቶችን/የልጃገረዶችን ኢኮኖሚያዊ ብቃት መደገፍ እና እነዚህን አደጋዎች ለመቅረፍ ዕድሎችን ማሳደግ አለበት።

አስተማማኝ ገቢ ካለመኖር የተነሳ የሚፈጠር ማህበራዊ መገለል ለግለሰቧ የስነ-ልቦና ጤንነት እና የማንነት ቀውስ መንስኤ ብቻ ሳይሆን የህልውና አደጋ ሊያስከትል ይችላል። በኢትዮጵያ ገጠራማ አካባቢዎች እና በድርቅ፣ በረሃብ እና በረጅም ጊዜ የተወሳሰቡ ቀውሶች የተጠቁ ክልሎች ውስጥ ጋብቻ የሴቶች እና ልጃገረዶች የህልውናቸው ማቆያ ስልት ነው።

በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ የሚሰሩ የሰብአዊ እና የልማት ድርጅቶች የልጃገረዶችን/የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ አቅም በማጎልበት የመብቶቻቸውን ግንዛቤ በማሳደግ ድርጅቱን ለማሻሻል የክህሎት ግንባታ ቅድሚያ መስጠት አለባቸው። የደህንነት አማራጮች ከሌሉ (ከጋብቻ ውጭ) የሴት ልጅ ግርዛት አስፈላጊ ነው የሚለውን እምነት መቀየር አይቻልም።

# ምንድን ነው የሚያስፈልገው?

## ቀጣይ እርምጃ

ከላይ እንደተገለፀው በኢትዮጵያ የተቀናጀ ትግበራ እና የፖሊሲ ምላሾች ሊፈቷቸው የሚገባቸው አምስት ዋና ዋና ተግዳሮቶች አሉ። የድርጊቱን ስርጭት ለመቀነስ እና በመጨረሻም ተወግዶ ለማየት የሚሰሩ በርካታ ድርጅቶች ቢኖሩም፣ እነዚህን ግቦች በብቃት ለመድረስ የሚከተሉት ገጽታዎች መስተካከል አለባቸው።

- በኢትዮጵያ የሴት ልጅ ግርዛትን ለመከላከል የፋይናንስ ምንጮችን **ማሳደግ**፣ እድገትን ለማፋጠን ዘርፈ ብዙ ምላሽ መስጠት
- እንደ አካባቢያዊ የስርጭት መጠን **ዒላማ** ማድረግ፤
- የንዑስ ክልላዊ መረጃዎችን **መሰብሰብ** እና **ጥቅም ላይ ማዋል፤**
- በእያንዳንዱ ማህበረሰብ ውስጥ ካለው አሠራር ጋር ከተያያዙ **ልዩ** ሁኔታዎች እና አውድ ጋር መሰተፍ፤
- ስለ ሴት ልጅ ግርዛት አመለካከቶችን እና እምነቶችን ለመመርመር በተዘዋዋሪ መንገድ በመጠቀም የምርምር ዘዴዎችን **ማሻሻል**፤
- ወንዶችንና ወጣት ወንዶችን፣ የሃይማኖት መሪዎችን እና ተደማጭ የማህበረሰብ አባላትን በማሳተፍ ያልተገረዙ ሴቶችን እና ልጃገረዶችን ከማህበራዊ መገለል አደጋን **መቀነስ፤**
- የማህበረሰብ ውይይቶችን እና የክህሎት ስልጠናዎችን ከግንኙነት ጋር **በማቀናጀት** የሴት ልጅ ግርዛትን ግንዛቤ ማሳደግ፣
- የሴቶች እና ልጃገረዶች ኢኮኖሚያዊ እድሎችን **ማጠናከር** እና **ማሳደግ**።

## ምክሮች

ግኝቶቻችንን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚከተሉትን እንመክራለን፡

- አክቲቪስቶች እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት የኢትዮጵያ መንግሥት የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስወገድ ያለውን ቁርጠኝነት ለማፋጠን የሚመድበውን በጀት/ገንዘብ እንዲያሳድግ ግፊት ማድረግ።
- ተመራማሪዎችና ፈጻሚ ድርጅቶች የአህጉራዊ መረጃዎችን አቅርቦት ለማሻሻል፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ የፕሮግራም አወጣጥን ለማሳወቅ የበኩላቸውን አስተዋፅዖ ያደርጋሉ።
- ተጽዕኖ ፈጣሪ የሆኑ የማህበረሰቡ አባላትን፣ የሃይማኖት መሪዎችን፣ ወንዶችን ከሴቶች እና ልጃገረዶች ጋር በማሳተፍ፣ የማህበረሰብ ውይይቶች ስልቶችን መጠቀም፤
- ሰዎች ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ያላቸውን እምነትና አመለካከት በትክክል ለመመርመር በተዘዋዋሪ የጥያቄ ዘዴዎችን ለሚጠቀሙ ጥናቶች ድጋፍ መስጠት። እና

- የሴቶችና ልጃገረዶች ኢኮኖሚያዊ አቅምን ማጎልበትና ማጠናከር ግርዛትን ለማስወገድ የሚሰሩ ድርጅቶችን የማጠናከር እና ልጃገረዶች/ሴቶች የመወሰን ዕድላቸውን ለመጨመር እና በማህበራዊ መገለል ላይ ያላቸውን ስጋት ለመቀነስ ከሚረዱ ዘዴዎች ጋር ተቀናጅተው እንዲሰሩ ማድረግ።

## ተግባራዊ ጥሪ

### ለኢትዮጵያ መንግስት

የኢትዮጵያ መንግስት የሚከተለውን እንዲያደርግ እንጠይቃለን።

- የ10% ቁርጠኝነት ላይ ለመድረስ እና በኢትዮጵያ የሴት ልጅ ግርዛትን ለማጥፋት በብሔራዊ ወጪ የተከፈለው ፍኖተ ካርታ እና የሴት ልጅ ግርዛት 2012-2016 ዓ.ም መሰረት የበጀት/ሀብት ድልድል ማሳደግ። እና
- በሴት ልጅ ግርዛት አዝማሚያ (ለምሳሌ በዞንና በወረዳ ደረጃ) አህጉራዊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ድጋፍ ማድረግ።

### ባለድርሻ አካላት

በኢትዮጵያ ለሚገኙ ለመንግስት አካላት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ለሌሎችም ባለድርሻ አካላት የምቀርበው ጥሪ፡-

- መንግስት እና የውጭ ለጋሽ ድርጅቶች ገንዘብ እንዲመድቡ እና ያለእድሜ ጋብቻን እና የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቆም ብሄራዊ ወጪ የተደረገበት ፍኖተ ካርታ (2012-2016 ዓ.ም) እነዲተገበር **እንዲሚገቱ፤**
- ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ያሉ አመለካከቶችን እና እምነቶችን በመቀየር የረዥም ጊዜ ስራ ላይ ለተሰማሩ መሰረታዊ እና ሌሎች ድርጅቶች ሃብት እንዲከፋፈል **እንዲሚገቱ**።
- ድርጊቱ በሚበዛባቸው በታዎች ላይ ጣልቃ ለመግባት ተዘጋጅቶ ያለውን መረጃ መጠቀም፤
- ውጤታማ ክትትል እና ጣልቃገብነት ግምገማ በማድረግ በአህጉራዊ መረጃ ላይ ያለውን ክፍተት ለመሙላት መስራት;
- በመጀመሪያ ደረጃ የሴት ልጅ ግርዛትን ከሚያፋጥኑ ልዩ ሁኔታዎች እና ያልተገረዙ ልጃገረዶች የሚያጋጥሟቸውን ማህበራዊ የመገለል አደጋዎች ለመረዳት መፈለግ፤ እና በሁለተኛ ደረጃ ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት፤ እና
- የድርጅታቸውን እና የውሳኔ ሰጪነት ስልጣናቸውን ለማሳደግ በዕቅድ የሴቶች እና ልጃገረዶችን ኢኮኖሚ ማጠናከር እና ማጎልበትን እንዲያካትቱ።

**ለጋሾች**

ለጋሾች ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር በመተባበር የህፃናት ጋብቻን ለማስቆም እና 2012-2016 ዓ.ም ለወጣው ፍኖተ ካርታ የገንዘብ ድጋፍ እንዲያደርጉ እና የሚከተሉትን ፕሮግራሞች እና ውጥኖች በንቃት እንዲደግፉ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

- ቀጥተኛ ያልሆኑ የጥያቄ ዘዴዎችን በመጠቀም ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ትክክለኛ አመለካከት እና እምነት የማወቅ ዘዴን ለማረጋገጥ ዓላማ ያድርጉ; እና
- በማህበራዊ መገለል ምክንያት ሴቶች/ልጃገረዶች ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን ለመቀነስ እና ውሳኔያቸውን እንዲለማመዱ እድሎችን ለማሻሻል በሚሰሩበት ወቅት ልዩ የሆኑ ብሄሮች እና ባህላዊ ሂደቶች ጋር መሳተፍ።

# References

**Recommended citation:** Orchid Project and 28 Too Many (2023) *FGM/C in Ethiopia: Update Key Findings*. Available at https://www.fgmcri.org/country/ethiopia/.

*Please note that, throughout the citations and references in this report, the following abbreviations apply.*

**'DHS 2016'** refers to Central Statistical Agency/CSA/Ethiopia and ICF (2016) *Ethiopia Demographic and Health Survey 2016*. Addis Ababa, Ethiopia, and Rockville, Maryland, USA: CSA and ICF. Available at https://dhsprogram.com/pubs/pdf/FR328/FR328.pdf.

**'DHS 2011'** refers to Central Statistical Agency/Ethiopia and ICF International (2012) *Ethiopia Demographic and Health Survey 2011*. Addis Ababa, Ethiopia: Central Statistical Agency and ICF International. Available at https://dhsprogram.com/pubs/pdf/FR255/FR255.pdf.

**'DHS 2005'** refers to Central Statistical Agency/Ethiopia and ORC Macro (2006) *Ethiopia Demographic and Health Survey 2005*. Addis Ababa, Ethiopia: Central Statistical Agency/Ethiopia and ORC Macro. Available at https://dhsprogram.com/pubs/pdf/FR179/FR179[23June2011].pdf.

**'DHS 2000'** refers to Central Statistical Authority/Ethiopia and ORC Macro (2001) *Ethiopia Demographic and Health Survey 2000*. Addis Ababa, Ethiopia: Central Statistical Authority/Ethiopia and ORC Macro. Available at https://dhsprogram.com/pubs/pdf/FR118/FR118.pdf.


1 - DHS 2000, p.33.
- DHS 2005, p.253.
- DHS 2016, p.321.

2 - DHS 2000, p.33.
- DHS 2016, p.321.

3 - DHS 2000, p.33.
- DHS 2016, p.321.

4 United Nations Children's Fund (2020) *A Profile of Female Genital Mutilation in Ethiopia*. UNICEF. New York. Available at https://www.unicef.org/ethiopia/reports/profile-female-genital-mutilation.

5 DHS 2016, p.321.

6 DHS 2016, p.321.

7 DHS 2016, p.323.

8 *DHS Program STATcompiler* (2023) [website]. https://www.statcompiler.com/en/.

9 DHS 2016, p.325.

10 WHO Africa (2017) *Ethiopia bans medicalization of female genital mutilation (FGM)*, 31 January. Available at https://www.afro.who.int/news/ethiopia-bans-medicalization-female-genital-mutilation-fgm#:~:text=As%20part%20of%20its%20endeavors%20to%20ensure%20the,public%20and%20private%20medical%20facilities%20in%20the%20country.

11 UNICEF (2021) The Medicalization of FGM In Kenya, Somalia, Ethiopia and Eritrea, p.13. Available at https://www.unicef.org/esa/media/8866/file/The-Medicalization-of-FGM-2021.pdf.

12 DHS 2016, p.327.

13 DHS 2016, p.326.
14 DHS 2016, p.327.
15
- Mhairi A. Gibson, Eshetu Gurmu, Beatriz Cobo, María M. Rueda and Isabel M. Scott (2018) 'Indirect questioning method reveals hidden support for female genital cutting in South Central Ethiopia', *PLoS ONE*, 13(5). https://doi.org/10.1371/journal.pone.0193985.
- Elisabetta De Cao and Clemens Lutz (2018) 'Sensitive Survey Questions: Measuring Attitudes Regarding Female Genital Cutting Through a List Experiment', *Oxford Bulletin of Economics and Statistics*, 80, pp.871–892. https://doi.org/10.1111/obes.12228.

16 DHS 2016, p.321.
17 Elizabeth Presler-Marshall, Nicola Jones, Erin Oakley, Rebecca Dutton, Sarah Baird, Workneh Yadete and Yitagesu Gebeyehu (2022) *Exploring the diversity of FGM/C practices in Ethiopia: Drivers, experiences and opportunities for social norm change*. London: Gender and Adolescence: Global Evidence. Available at https://www.gage.odi.org/publication/exploring-the-diversity-of-fgm-c-practices-in-ethiopia-drivers-experiences-and-opportunities-for-social-norm-change.
18 *DHS Program STATcompiler* (2023) [website]. https://www.statcompiler.com/en/.
19 *DHS Program STATcompiler* (2023) [website]. https://www.statcompiler.com/en/.
20 DHS 2016, pp.322 & 323.
21 UN Office of the High Commissioner for Human Rights (2021) *Report of the Ethiopian Human Rights Commission (EHRC)/Office of the United Nations High Commissioner for Human Rights (OHCHR) Joint Investigation into Alleged Violations of International Human Rights, Humanitarian and Refugee Law Committed by all Parties*. ReliefWeb. Available at https://reliefweb.int/report/ethiopia/report-ethiopian-human-rights-commission-ehrcoffice-united-nations-high-commissioner.
22 Al Jazeera (2022) *UN: Warring sides committing atrocities in Ethiopia's Tigray*, 19 September. Available at https://www.aljazeera.com/news/2022/9/19/un-warring-sides-committing-atrocities-in-ethiopias-tigray.
23 The Independent (2023) *Ethiopia church split resolved amid social media suspension*, 16 February. AP News Wire. Available at https://www.independent.co.uk/news/ap-oromia-ethiopia-nairobi-kenya-b2283730.html.
24 Federal Democratic Republic of Ethiopia, Ministry of Women, Children and Youth (2019a) *Summary: National Costed Roadmap to End Child Marriage and FGM/C 2020–2024*. Available at https://ethiopia.un.org/sites/default/files/2019-09/Roadmap%20to%20end%20child%20marriage%20and%20FGM%20summary%20Unicef%20.pdf.
25 Ms Berhane Ras-Work (2009) *Legislation to Address the Issue of Female Genital Mutilation (FGM)*, p.9. United Nations Division for the Advancement of Women and United Nations Economic Commission for Africa. Available at https://www.un.org/womenwatch/daw/egm/vaw_legislation_2009/Expert%20Paper%20EGMGPLHP%20_Berhane%20Ras-Work%20revised_.pdf.
26 Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Women, Children and Youth (2019b) *National Costed Roadmap to End Child Marriage and FGM/C 2020–2024*, p.72. Available at https://www.unicef.org/ethiopia/media/1781/file/National%20Roadmap%20to%20End%20Child%20Marriage%20and%20FGM.pdf.
27 Federal Democratic Republic of Ethiopia, Ministry of Women, Children and Youth (2019a), *op. cit.*
28 Federal Democratic Republic of Ethiopia, Ministry of Women, Children and Youth (2019b), *op. cit.*
29 Federal Democratic Republic of Ethiopia, Ministry of Women, Children and Youth (2019b), *op. cit.*
30 UNICEF (2020) *A Profile of Female Genital Mutilation in Ethiopia*, p.5. New York: UNICEF. Available at https://www.unicef.org/ethiopia/reports/profile-female-genital-mutilation.
31 Mhairi A. Gibson, Eshetu Gurmu, Beatriz Cobo, María M. Rueda and Isabel M. Scott (2018), *op. cit.*
32 Elisabetta De Cao and Clemens Lutz (2018), *op. cit.*

33 Tesfahun Taddege Geremew, Muluken Azage and Endalkachew Worku Mengesha (2021) ‘Hotspots of female genital mutilation/cutting and associated factors among girls in Ethiopia: a spatial and multilevel analysis’, *BMC Public Health*, 21(186). Available at https://doi.org/10.1186/s12889-021-10235-8.

34 Elizabeth Presler-Marshall, Nicola Jones, Erin Oakley, Rebecca Dutton, Sarah Baird, Workneh Yadete and Yitagesu Gebeyehu (2022) Exploring the diversity of FGM/ C practices in Ethiopia. Drivers, experiences and opportunities for social norm change. London: Gender and Adolescence: Global Evidence. Available at https://www.gage.odi.org/publication/exploring-the-diversity-of-fgm-c-practices-in-ethiopia-drivers-experiences-and-opportunities-for-social-norm-change.

35 Olusola Oladeji, Julie Battle and Haithar Ahmed (2022) ‘Key Factors, Drivers and Gatekeepers of Female Genital Mutilation in Ethiopia: A Meta-synthesis of National and Regional Studies’, *Advances in Research*, 23(6), pp.30–37. Available at https://www.researchgate.net/publication/364356903_Key_Factors_Drivers_and_Gatekeepers_of_Female_Genital_Mutilation_in_Ethiopia_A_Meta-synthesis_of_National_and_Regional_Studies.

## Images

*Cover:* Tran Qui Thinh (undated) *Woman walking on the street in Harar* [cropped]. Shutterstock ID 1265835001.

***Please note the use of this girl’s image does not imply that she has, nor has not, undergone FGM/C.***

© Orchid Project & 28 Too Many 2023

research@orchidproject.org